# ሎተሪና ሊስትሮ

በሊስትሮ ሞያ ጫማ ላጸዳለሁ፣
ያልፍልኛል ብየም ሁሌ እለፋለሁ፣
ብሎም ያን ሎተሪ ዘወትር እገዛለሁ...
ይኸው እኖራለሁ!

ይደርሰኛል እያልኩ ሎተሪ መግዛቴ፣
ከችግር እንዳመልጥ ብዙ መመኘቴ፣
በሎተሪ መክሰር ብልጠት/ሞኝነቴ...
ባዶ እጄን መቅረቴ!

ወትሮ የሚታየኝ ጫማውን ስጠርግ፣
ሃብታም ሰው ተብየ ባለ መዓርግ፣
ቀንጆ ሚስት ሳገባ በቀለጠ ሰርግ...
ይበለው ለደግ!

ያሸናፊው ወሬ በሬድዮ ሲነዛ፣
ዕድሌ ሆነና ቀርፋፋ፣ ፈዛዛ፣
ሎተሪ አልደርስ አለኝ ብገዛ፣ ብገዛ...
ምን-አባቱ፣ በዛ!

በሊስትሮነቴ ጫማ እየጠረግሁ፣
ያልፍልኛል ብየም ተስፋ እያደረግሁ፣
ሲርበኝም ሆዴን ሽምብራ እየመረግሁ...
ዓዘቅት ተረገረግሁ!

ሃብታም አልወለደኝ፣ ሎተሪ አልደረሰኝ፣
ዘወትር እንደዚህ ሆዴን ከሚብሰኝ፣
ማርቸዲሱ ድጦ አፈር ባነከሰኝ...
አብዝቶ እንዲክሰኝ!

ሎተሪ እገዛለሁ ዛሬም እንደገና፣
ከቶ ምንም ቢሆን ተስፋ አልቆርጥምና፣
ባይደርሰኝም ይቅር፣ ግድ የለም፣ ደህና...
የት-አባቱንስና!

ገ/ኢ. ጐርፉ። Jan. 2005